በውኑ ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ አላትን?

ቴዎድሮስ ደመላሽ

መግቢያ

ሰማንያ አሐዱ ምንድን ነው?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው ዓለም የተለየ የመጽሐፍ ቅዱሰ አቀባበል ያላት መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህም ‹‹ሰማንያ አንዱን መጻሕፍት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተጻፉ ከቀጥር ሳታንድል በእምነት ተቀብላ የምትገለገልባቸው ብቸኛዋ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን››፣[1] ‹‹የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሌላው ዓለም የሌለውን ከፍተኛውን የመጽሐፍ ቀጥር ይዛ ትገኛለች››[2]፣ ‹‹በዓለም ላይ ብቸኛዋ የ81 ቅዱሳት መጻሕፍት ባለቤት...››[3] መሆኗን የሚሰጡትን ምስክርነቶች መመልከት ይቻላል።

ቤተ ክርስቲያንን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የለያት ይህ መጽሐፍ ምንድን ነው? ቢባል ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ ያለው የመጻሕፍት ቀጥር ብዛት ከቤተ ክርስቲያናችን ያነሰ ነው ማለት ነው።[4] ይህ እንዲሆን ያደረገው ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ፤ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል፣መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ፣ መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ 1ኛ መቃብያን፣ 2ኛ መቃብያን፣ 3ኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ ጸሎተ ምናሴ፣ ተረፈ ኤርምያስ፣ መጽሐፈ ሶስና፣ መጽሐፈ ባሮክ፣ መጽሐፈ ጦበት፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ፣ ተረፈ ዳንኤል፣ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣ መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የተሰኙት መጻሕፍት መካተት አለባቸው ስትል፤ በዐዲስ ኪዳን ደግሞ ሥርዓተ ጽዮን፣ ትእዛዝ፣ ግጽው፣ አብጥሊስ፣ 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ ቀሌምንጦስ፣ ዲድስቅልያ የተሰኙት መጻሕፍት የመጽሐፉ አካል መሆን አለባቸው ብላ ታምናለች።

ቀደም ሲል ከላይ ከተዘረዘሩት መጻሕፍት መካከል፤ ጸሎተ ምናሴ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ፣ ተረፈ ኤርምያስ ትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ፣ መጽሐፈ ሶስና፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅና ተረፈ ዳንኤል ትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ገብተው፣ 2ኛ እና 3ኛ መቃብያን እንደ አንድ መጽሐፍ የሚቁጠሩ ሲሆን ሌሎቹ ግን በራሳቸው የሚቆሙ ናቸው። ይህ ነው ሰማንያ አሐዱ ተብሎ የሚጠራው።

---

[1] ዝኒ ከማሁ ገጽ 3። ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (መምህር) ጸረ ማርያሞች አታወናብዱ፣ (ዐዲስ አበባ፣ 1992) ገጽ 18 - አጽንዖት የግል።

[2] ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት (1963)፣ ገጽ 43 - አጽንዖት የግል።

[3] ማኅበረ ቅዱሳን፣ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ (ሐምሌ 1-15 2004) ገጽ 2። ብርሃነ ሥላሴ አስፋው (መምህር) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመከራ ጉዞ (በታሪክ ውስጥ) (2006)፣ ገጽ 78 - አጽንዖት የግል።

[4] ምንም እንኳ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከቤተ ክርስቲያናችን ያነሰ የመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥር ቢኖራቸውም በአቀባበል ደረጃ ግን ወጥ የሆነ ነገር የሌለ መሆኑ ይታያል። ‹‹በግብፅ ኦርቶዶክስ 45፣ በሦርያ ኦርቶዶክስ 50፣ በሕንድ ኦርቶዶክስ 52፣ በአርመን ኦርቶዶክስ 44፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ 89 መጻሕፍት ተቀባይነት እንዳላቸው መምህር ቸርነት አበበ በሠንጠረዥ አሳይተዋል። አቶ ሚልዮን በለጠ ‹በየአገሩ ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት ጠይቁ እንደተረዳሁት› ብለው ባሰፈሩት የሕንድ ኦርቶዶክስ 79፣ የሩሲያ ኦርቶዶክስ 77፣ የአርመን ኦርቶዶክስ 75፣ የግብፅ ኦርቶዶክስ 73 መጻሕፍትን እንደሚቀበሉ አስነብበዋል። ከዚህም ሌላ የግሪክ ኦርቶዶክስ 76/77፣ ካቶሊክ 73 ወንጌላውያን 66 መጻሕፍትን ይቀበላሉ። ከዚህም በመነሣት ቤተ ክርስቲያናችን ከወንጌላውያንና ከካቶሊክ ብቻም ሳይሆን ከእኅት አብያተ ክርስቲያናትም ጋር ተመሳሳይ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አቈጣጠር እንደሌላት ከዚህ ማስተዋል ይቻላል። ለዚህም ነው በተደጋጋሚ ከሌላው ዓለም የተለየ የመጽሐፍ ቀጥር እንዳላት መነገሩ፤ ምክንያቱ ግን ምን ይሆን?›› (ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን (2010 - ሦስተኛ ዕትም) ገጽ 1-18)።

ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ አላትን?

የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሁለት መንገዶች ይኖራሉ፤ እነርሱም ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ ናቸው ብላ የምታምንባቸውን መጻሕፍት አሳትማ እንደ ሆነ መፈለግ እና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሰማንያ አሐዱ የሚሏቸው መጻሕፍት የትኞቹ እንደ ሆኑ ማሳየት ናቸው። ከመጀመሪያው በመጀመር እነዚህን ሁለት ነጥቦች በመረጃ ከዚህ በታች ለማሳየት ተሞክሯል።

፩

ቀደም ሲል እንደተባለው ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ ናቸው ብላ የምታምንባቸውን መጻሕፍት አሳትማ እንደ ሆነ መፈለግ ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ የሚባል መጽሐፍ የሌላት መሆኑን ለማሳየት ይረዳል። በዚህ ጥረት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሦስት ጊዜ ሰማንያ አሐዱ ብላ ስም ያወጣችላቸውን መጻሕፍት ማሳተሟን ማየት ይቻላል። ነገር ግን ሦስቱም መጻሕፍት ‹ሰማንያ አሐዱ› ይባሉ እንጂ ሰማንያ አንድ መጻሕፍት አለመሆናቸውን ከዚህ በታች መመልከት ይቻላል።

በመጀመሪያው የታተመው የ1947 ዓመተ ምሕረት ዕትም በውስጡ የያዘው ሰማንያ አንድ መጻሕፍት ዝርዝር ሳይሆን 71 ብቻ ነው። ይሄውም ሐዲስ ኪዳን ላይ መጨመር የነበረባቸው 8 መጻሕፍትና[5] ብሉይ ኪዳን ውስጥ መካተት ያለበትን 1 መጽሐፍ[6] በድምሩ ዘጠኝ መጻሕፍት በዘነጋ መልኩ ነው።

ለሁለተኛ ጊዜ ሰማንያ አሐዱ ተብሎ የታተመው መጽሐፍ በ1980 ዓመተ ምሕረት ለንባብ የበቃ ሲሆን የማውጫው ዝርዝር 85 መጻሕፍትን ይዟል። ይህም ቢሆን ቀደም ሲል የቀረቡትን 9 መጻሕፍት ሳይካትት ነው። እንደ ፍትሐ ነገሥት አቈጣጠር ግን እነዚህ መጻሕፍት የግድ መግባት አለባቸውና እነርሱ ሲካተቱ 94 መጻሕፍት እንጂ 81 አይመጣም። ሐሳቡን ግልጽ ለማድረግ በሒሳብ ስሌት እናስቀምጠው፦

85 የመጻሕፍት ዝርዝር አለ
+ 9 የተዘነጉት መጻሕፍት ሲጨመሩ
94 መጻሕፍት ይመጣል።

ለሦስተኛ ጊዜ በ2000 ዓመተ ምሕረት የታተመው መጽሐፍ ማውጫው ላይ 81 መጻሕፍትን ይዘረዝራል። ነገር ግን ቀደም ሲል የተነሡትና በብሉይ ኪዳን መግባት የነበረበት ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን በዐዲስ ኪዳን መግባት የነበረባቸው ስምንቱ የሥርዓት መጻሕፍት ሳይካተቱ ነው። ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና የተቀበለቻቸው የብሉያትና የዐዲሳት መጻሕፍት ቍጥር ሰማንያ አንድ ነው›› የሚለው ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ

[5] እነዚህ ስምንት መጻሕፍት የሥርዓት መጻሕፍት የሚባሉ ሲሆን ዝርዝራቸውም፦ ሥርዓተ ጽዮን፣ ትእዛዝ፣ ግጽው፣ አብጥሊስ፣ 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ ቀሌምንጦስ፣ ዲድስቅልያ ናቸው።

[6] መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን።

ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት›› የተሰኘው መጽሐፍ ዝርዝሩን ሲያስቀምጥ እነዚህ ዘጠኝ መጻሕፍትንም አካቶ በማስቀመጥ በመሆኑ መግባታቸው አማራጭ የሌለው ግዴታ ነውና እነርሱ ሲገቡ 90 መጻሕፍት ይመጣል።[7] ታዲያ ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ የሚባለው መጽሐፍ አላትን? ይህ ጥያቄ የእኔ ብቻ ሳይሆን የማኅበረ ቅዱሳን አመራር አካል የሆኑት የቸርነት አበበም ጭምር ነው። እርሳቸው ‹‹መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ›› በሚለው መጽሐፋቸው ‹‹በተለያዩ ጊዜያት ማለትም በ1918፣ 1929፣ 1947 (1953) እና 1980 ዓመተ ምሕረት[8] የታተሙት መጽሐፍ ቅዱሶች ዝርዝር አንዱም ግልጽ በሆነና ቁርጥ ባለ ሁኔታ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ አያሳይም›› የሚል ሐሳብ አቅርበዋል።[9]

፪

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሰማንያ አሐዱ የሚሏቸው መጻሕፍት የትኞዎቹ ናቸው? የሚለውን በመመልከት ይሆናል።

ከዚህ በታች የቀረበው ዝርዝር ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አንድ መጻሕፍትን እቀበላለሁ ትበል እንጂ በሊቃውንትም ሆነ በሌሎች አገልጋዮች በኩል ይፋ የሆኑት የጽሑፍ መልእክቶች እንደሚናገሩት ሰማንያ አንዱን መጻሕፍት በርግጠኝነት እነዚህ ናቸው ለማለት እንዳልተቻለ ይጠቁማል።

- ቅዱስ ሲኖዶስ አዘጋጅቶት በ1975 ዓመተ ምሕረት ያሳተመው አነስተኛ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን ‹‹... 81 ቅዱሳት መጻሕፍት አሏት›› የሚለውን አስነብቦ ወደ ዝርዝሩ ሲገባ ግን መጽሐፈ ኩፋሌን፣ ሄኖክን፣ ዕዝራ ካልእና ዕዝራ ሱቱኤልን እንዲሁም 3ኛ መቃብያንን ከቍጥር ውጪ አድርጓቸዋል።[10]
- ‹‹ከቤተ ክርስቲያናችን ታላላቅ ሊቃውንት መካከል አንደኛው›› ናቸው የሚባልላቸው አለቃ አያሌው ታምሩ ከዚህ ሐሳብ ጋር ይስማማሉ፤ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን ጨምረው ከቍጥር ውጭ በማድረግ መጠናኛ ልዩነት አሳዩ እንጂ።[11]
- ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት›› የተሰኘውና ቤተ ክርስቲያን እምነቴን ያሳይልኛል ብላ ያሳተመችው መጽሐፍ 81 የመጻሕፍት ዝርዝርን ሲያስቀምጥ ጥበበ ባሳርንና መጽሐፈ ባሮክን ግን ረስቷቸዋል።[12]
- ‹‹የቤተ ክርስቲያን ጸሎት›› የተሰኘው መጽሐፍ 80 የመጻሕፍት ዝርዝር ያስቀምጣል። ዝርዝሩ ሲታይ ግን ከብሉይ ኪዳን 3ኛ መቃብያንን እና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን፣ ከዐዲስ ኪዳን ደግሞ ስምንቱን የሥርዓት መጻሕፍትን ከቁጠራ ውጪ ያደርጋል።[13]

---

[7] ገጽ 42-45።

[8] በ2000 ስለታተመው ሰማንያ አሐዱ አስተያየት ያልሰጡት ምናልባት ‹‹ግልጽ በሆነና ቁርጥ ባለ ሁኔታ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞች እንደ ሆኑ›› አመላክቷል ብለው ይሆን?

[9] ገጽ 43።

[10] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ (ዐዲስ አበባ፣ 1975) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲን አጭር የታሪክ የሃይማኖት የሥርዓት መጽሐፍ ገጽ 68-71።

[11] ሰይፍ የኅትመት እና ማስታወቂ ሥራ ድርጅት፣ ሐዋርያ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ሰኔ-ሐምሌ 1991፣ ገጽ 8።

[12] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (ዐዲስ አበባ፣ ሐምሌ 1988) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤቱ ክርስቲን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት ገጽ 42-45።

[13] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ የቤተ ክርስቲያን ጸሎት (ዐዲስ አበባ፣ 1996) ገጽ 97-99።

- የ‹‹ዓምደ ሃይማኖት›› መጽሐፍ አዘጋጅ፤ ሦስት መጻሕፍትን ማለትም፤ መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ እና እንደ አንድ የሚቈጠሩትን 2ኛ እና 3ኛ መቃብያንን፤ እንዲሁም መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን በማጉደል ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱን ትቀበላለች ይላሉ፡፡[14]
- አቶ ዓሥራት ገብረ ማርያም ‹‹ተከራካሪዎች ያልተቀበሉአቸው መጻሕፍት›› በሚለው ርዕሳቸው ስር ‹‹መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ ጥበበ ሰሎሞን፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ አንደኛ እና ሁለተኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ባሮክ እንዲሁም ተረፈ ዳንኤልና ተረፈ አስቴር››ን ሲያስቀምጡ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣ ዕዝራ ካልእና ዕዝራ ሱቱኤል፣ ሦስተኛ መቃብያንና መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን አላካተቷቸውም፡፡[15]
- ‹‹መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት›› የተሰኘው መጽሐፍ ደግሞ፤ መጽሐፈ ነህምያና መጽሐፈ ዕዝራን (ሁለቱ መጻሕፍት እንደ አንድ ነው የሚቈጠሩት) እና ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን ያጎድላል፡፡[16]
- የቤተ ክርስቲያን ልሳን የነበረውና በ1982 ዓመት ምሕረት የታተመው ‹‹ትንሣኤ›› መጽሔት ‹‹ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሄኖክንና ኩፋሌን ትቀበላቸዋለች›› ይልና ‹‹ግን እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ከ81 ጋር አይቈጠሩም›› በሚል ከቍጥር ያወጣቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ 3ኛ መቃብያንን ሳይጠራው አልፏል፡፡[17]
- ዐሥራት ከበደ የተረጎመው ‹‹መጽሐፈ ጦቢት›› የተሰኘው መጽሐፍ 3ኛ መቃብያንን፣ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮንን፣ ሄኖክንና ኩፋሌን አይቈጥራቸውም፡፡[18]
- ‹‹እንድትጸኑባቸው ያዘዝናችሁ መጻሕፍት እነዚህ ናቸው፡፡ ከሐድያን ከአስቀመጧቸው የሐሰት መጻሕፍት የወሰደና ንጽሕት የሆነች የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደ ሆነች አድርጎ ሕዝብን ለማሳሳት ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ያገባ ሰው ቢኖር ይለይ›› የሚለው ‹‹ፍትሐ ነገሥት›› ደግሞ እንደ ‹‹መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት›› ሁሉ መጽሐፈ ነህምያንና መጽሐፈ ዕዝራን ትታቸዋል፡፡ መጽሐፈ ኩፋሌን ‹‹ነውር ስለ ተገኘበት›› ብሎ ከቍጥር ሲያስወጣው፤ ሄኖክንም እንዲሁ ሊቆጠር እንደማይገባው በግልጽ ይናገራል፡፡[19] የትኛውን ነው መቀበል የሚገባው? የትኛውስ ነው ሰማንያ አሐዱን የሚያመለክተው አቈጣጠር? እስከ አሁን ሊቃውንቱ እንኳ ተስማምተው ይህ ነው ሰማንያ አሐዱ ለማለት አቅም ስላላገኙ ቤተ ክርስቲያን ሰማንያ አሐዱ የላትም!!!

ሐሳቡን የተሻለ ለመረዳት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያገኙት መጻሕፍት የትኞዎቹ ናቸው? የሚለውን መመልከቱ ይጠቅማል፤ ለዚህም ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ ይረዳል ተብሎ ይታሰባል፤

---

[14] ብርሃኑ ጎበና፣ ዓምደ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ ሚዝያ 1995) ገጽ 35-36፡፡

[15] ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ ትምህርት መለኮት (2005) ገጽ 128፡፡ ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ ፍኖተ ብርሃን (ዐዲስ አበባ፣ 1993) ገጽ 147-153፡፡

[16] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት (ዐዲስ አበባ፣ 1988) መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 145-147፡፡

[17] (በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስበከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ትንሣኤ መጽሔት መጋቢት/ሚያዝያ 1982 ጽ 1 እና 11፡፡

[18] አሥራት ከበደ (ትርጉም)፣ መጽሐፈ ጦቢት (ዐዲስ አበባ፣ 2005) ገጽ 13-14፡፡

[19] መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት (1994)፣ ገጽ 57፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ፍትሐ ነገሥት (ዐዲስ አበባ፣ 1995 ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ) ገጽ 43፡፡

የተጨማሪዎቹ መጻሕፍት ዝርዝር	የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. አጭር የሃይማኖት የሥርዓት መጽሐፍ	ትንሣኤ መጽሔት	የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. እምነት ሥርዓተ አምልኮ ትና የውጭ ግንኙነት	መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ	መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት	አለቃ አያሌው ታምሩ	ዓሥራት ገብረ ማርያም	ፍትሐ ነገሥት	የቤተ ክርስቲያን ጸሎት	ዐሥራት ከበደ
መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል	×	✓	✓	×	✓	×	×	✓	✓	✓
መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ	×	✓	✓	✓	✓	×	×	✓	✓	✓
መጽሐፈ ጦቢት	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ዮዲት	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
1ኛ መቃብያን	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
2ኛ መቃብያን	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
3ኛ መቃብያን	×	×	✓	×	✓	×	×	✓	×	×
መጽሐፈ ሲራክ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
ጸሎተ ምናሴ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
ተረፈ ኤርምያስ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ሶስና	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ባሮክ	✓	✓	×	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ጥበብ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
ተረፈ ዳንኤል	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓	✓
መጽሐፈ ኩፋሌ	×	×	✓	×	✓	×	×	×	×	×
መጽሐፈ ሄኖክ	×	×	✓	×	✓	×	×	×	×	×
መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን	✓	✓	✓	✓	×	×	×	×	✓	×

ሁሉም የተቀበሏቸው መጻሕፍት፤ መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ 1ኛ መቃብያን፣ 2ኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ሲራክ፣ ጸሎተ ምናሴ፣ ተረፈ ኤርምያስ፣ መጽሐፈ ሶስና፣ መጽሐፈ ጥበብ፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅና ተረፈ ዳንኤል ናቸው። ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ጸሎተ ምናሴ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ውስጥ፣ ተረፈ ኤርምያስ ትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ፣ መጽሐፈ ሶስና፣ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅና ተረፈ ዳንኤል ትንቢተ ዳንኤል ውስጥ እየገቡ የሚቈጠሩ በመሆናቸው ከ66ቱ መጻሕፍት ጋር አብረው ሊቈጠሩ የሚችሉት መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ 1ኛ መቃብያን 2ኛ መቃብያን፣ መጽሐፈ ሲራክ እና መጽሐፈ ጥበብ ብቻ ናቸው ማለት ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስያን የምቀበለው ሰማንያ አሐዱን መጽሐፍ ነው ትበል እንጂ መጽሐፉ የላትም ማለት ነው።

ጉርሻ፤ ቤተ ክርስቲያን ይቅርታ ትጠይቅ!

መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ለንባብ ከበቃበት ከ1879 ዓመተ ምሕረት (በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት)[20] ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁና ዓይነታቸው ልዮ ልዮ የሆኑ ዐሥር የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትሞች ለንባብ በቅተዋል።[21]

ከእነዚህ ዕትሞች ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የእኔ አይደሉምና አልጠቀምባቸውም የምትላቸው መጻሕፍት አሉ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡- በ1980 ዓመተ ምሕረት ከታተሙት ውስጥ አንዱን (ቀላል አማርኛ ተብሎ የታተመውን)፣ በ1985 ዓመተ ምሕረት የታተመውና ሕያው ቃል ተብሎ የሚታወቀውን ዐዲስ ኪዳን፣ በ1993 ዓመተ ምሕረት የታተመውንና ዐዲሱ መደበኛ ትርጕም ተብሎ የሚጠራውን፣ በ2000 ዓመተ ምሕረት ከታተሙት ውስጥ አንዱ የሆነውና ቀላል አማርኛ በሚል በድጋሚ የታተመውን እና በ2001 ዓመተ ምሕረት የታተመውንና ሙሉእ ሕይወት በሚል የሚጠራውን መጽሐፍ ቅዱስ።

ሌሎቹን መጻሕፍት ግን ስትገለገልባቸው እንደ ነበር ከዚህ በታች የሰፈረውን ይመልከቱ፤ በ1879 ዓመተ ምሕረት የታተመውን መጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ሥላሴ ከዚህ በታች የሰፈሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትሞች እስከሚያሳትሙ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ስትገለገልበት ነበር። በዐፄ ምንሊክ ጊዜ የታተመው የ1879 ዓመተ ምሕረት መጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎቱ እንዲያበቃ ያደረጉት ሁለት ነገሮች ናቸው። አንደኛው እትመቱ ቀጣይ አለመሆኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ ኃይለ ሥላሴ በስደት በነበሩበት ሰዓት ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ (ከ1928-1934 ዓመተ ምሕረት የታተመውን) አሳትመው ማምጣታቸው ነው። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ስለታተመው መጽሐፍ ዝግጅት ‹‹በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀውን መጽሐፍ ቅዱስ ምረቃ በዓል ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ ልዩ እትም›› የተሰኘው መጽሔት እንዲህ ይላል፤ ‹‹በ1923 ዓመተ ምሕረት በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ <u>በኢትዮጵያ ሊቃውንት ብቻ ከግእዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመው</u> መጽሐፍ ቅዱስ ከ1928-1934 ዓመተ ምሕረት ባሉት ዓመታት በሎንዶን በፎቶ ኦፌስት ታተመ። መጽሐፉ በግእዝና በአማርኛ ጎን ለጎን ስለ ተጻፈ ከትልቅነቱ የተነሣ በአራት ጥራዝ እንዲታተም ሆኗል››።[22] ልብ ይበሉ፤ ይህ መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው።

---

[20] እዚህ ጽሑፍ ላይ የተነሡት የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትሞች አይቶ ማረጋገጥ የወደደ አንባቢ ገበያ ላይ ሊያገኛቸው የሚችላቸውን ዕትሞች ናቸው። ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል አንዳንዶቹ ምንም እንኳ ዋጋቸው ውድ ቢሆንም ተፈልገው የሚገኙ ናቸው። ከእነዚህ መጻሕፍት ቀደም ሲል ታትመው የነበሩ መጻሕፍት ቢኖሩም እነርሱን ማግኘቱ አስቸጋሪ በመሆኑ ለመረጃነት አልተጠቀሱም።

[21] በ1879 የታተመው፣ ከ1928 - 1934 የታተመው፣ በ1953 የታተመው፣ በ1980 የታተሙት መጻሕፍት (ሁለት ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሶች)፣ በ1985 የታተመው - ዐዲስ ኪዳን ብቻ፣ በ1993 የታተመው፣ በ2000 የታተሙት መጻሕፍት (ሁለት ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሶች) እና በ2001 የታተመው።

[22] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን - (የታተመበት ዘመን ያልተጠቀሰ መጽሔት) ገጽ 17 - አጽንዖት የግል።

ይህም ቢሆን (ከ1928-1934 ዓመተ ምሕረት የታተመው) ግእዝና አማርኛ ሆኖ ስለ ታተመ፣ ትልቅ በመሆኑ በአራት ጥራዝ ነውና የወጣው በአንድ ላይ ማግኘት ስላልተቻለ፤ እንደገናም ደግሞ ኃይለ ሥላሴ የእትመት ማሽን አስመጥተው ማተሚያ ቤት አደራጅተው[23] መጽሐፍ ቅዱስ እንዲታተም ማድረጋቸው (የ1953 ዓመተ ምሕረት ዕትም) ከ1928-1934 ዓመተ ምሕረት በፎቶ ኦፊስት ታትሞ የነበረውን አገልግሎቱን ለዐዲሱ እትም እንዲለቅ አደረገው። ቀደም ሲል የተጠቀሰው መጽሔት ስለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ደግሞ የሚከተለውን ያስነብባል፤

> የካቲት 27 ቀን 1939 ዓመተ ምሕረት <u>ሰባት ኢትዮጵያዊያንና ሦስት የውጭ አገር ሊቃውንት</u> ያሉበት ጉባኤ <u>በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ</u> ተቋቁሞ በአባ አብርሃም የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥና ከዕርዕ ጋር በማነጻጸር የተሻለ ትርጉም አዘጋጅቶ በ1944 ዓመተ ምሕረት አቀረበ። ምክንያቱም የአባ አብርሃም ትርጉም ቃል በቃል እንጂ የአማርኛ ሰዋስው የጠበቀ አልነበረም። ይኸው ትርጉም በ1953 ዓመተ ምሕረት በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ። በዚህ ትርጉም ውስጥ በ1923 ዓመተ ምሕረት ከግእዝ ከተተረጎመው ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው ሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተካትተዋል።[24]

እስከዚህ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ስትጠቀምባቸው የነበሩት ዕትሞች ከቤተ ክርስቲያናችን እውቅና ውጪ የተዘጋጁ አለመሆናቸውን ማየት ይቻላል። በቀጥታ እጇ ያለበትና የራሷ ሊቃውንት መርምረውና ይሁን ብለው ያሳተሙት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በ1953 ዓመተ ምሕረት ታትሞ ለንባብ የበቃውና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እትም የሚባለው መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት መስጠቱን ሳያቆም በ1980[25] ዓመተ ምሕረት ትልቁ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሰማንያ አሐዱ ተብሎ የሚጠራው መጽሐፍ ታተመና ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን መጽሐፍ አሳትማለችና ሌሎቹን አትጠቀሙ ተባለ። ምንም እንኳ በተደጋጋሚ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበለው ሰማንያ አሐዱን ነውና ሌሎቹን አትጠቀሙ ቢባልም ሰማንያ አሐዱ ተብሎ የታተመው በ1953 ዓመተ ምሕረት ለንባብ ከበቃው ጋር አብረው እያገለገሉ በ2000 ዓመተ ምሕረት[26] ሰማንያ አሐዱ የሚል ስያሜ የተሰጠው መጽሐፍ የጎተመት ብርሃን አየ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ‹‹... ከዚህ በፊት ቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ ቅዱስን ከግእዝ ወደ አማርኛ [አስተርጉማ] የምታሳትምበት የገንዘብ ኃይል ስላልነበራት ነው።[27] መጻሕፍቶቹ ግን በየገዳማቱና በየአድባራቱ ይገኙ ነበር። በዚያን ጊዜ

---

[23] አሁን ብርሃንና ሰላም የሆነው ቀድሞ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት የነበረው።

[24] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ መጽሐፍ ቅዱስና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን - (የታተመበት ዘመን ያልተጠቀሰ መጽሔት) 17 - አጽንዖት የግል።

[25] በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ ታትሞ የነበረው።

[26] በአቡነ ጳውሎስ ዘመን ታትሞ የነበረው።

[27] ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ለማሳተም የገንዘብ አቅም አልነበራትም የሚለው ሐሳብ የሚገርም ሐሳብ ነው። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ማሳተም ብቻ አይደለም ከዚያም በላይ የማድረግ አቅም እንዳላት

አብዛኛው ምዕመናን የያዙት ይኸው ከእንግሊዘኛው የተተረጎመው ስድሳ ስድስቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። አሁን ግን የራሷ የሆነ[28] መጽሐፍ ቅዱስ ከግእዝ ወደ አማርኛው የተተረጎመ በመሆኑ...››[29] እሱን እንጂ ሌላውን መጠቀም ተገቢ አለመሆኑ እየተነገረ ይገኛል።[30]

በዚህ አባባል መሠረት ከ2000 ዓመተ ምሕረት በፊት ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራትም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ካልነበራት ደግሞ ትመራ የነበረው በመጽሐፍ ቅዱስ አልነበረም ማለት ነው። ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ትመራ የነበረ ከሆነ እንዴት ነው ቤተ ክርስቲያን ልትሰኝ የምትችለው?

ቀደም ሲል እንደተባለው በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ ሲታተም የነበረው መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሰዎች መድባ ኃይለ ሥላሴ ወጪውን ሸፍነው በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተዘጋጀ መሆኑን መግቢያው እንዲህ ይላል፤

> በእግዚአብሔር ቸርነት ለኢትዮጵያ ዙፋን ከተመረጥን ጀምሮ ሕዝባችን በትምህርትና በእውቀት እንዲያድግ ስንመራው በመንፈሳዊም በሥጋዊም ትምህርትና እውቀት እንዲያድግ አስበን በተቻለ ሁሉ ደክምንለት። ወደዚህም ግብ ለመድረስ አስቀድሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን ባማርኛ ማስተርጎምና አባዝቶ ማሳተም የሚያስፈልግ መሆኑን ስለ ተረዳን በ1910 ዓመተ ምሕረት ገና በአልጋ ወራሽነታችንና በእንደራሴነት ሳለን <u>ከኢትዮጵያ ሊቃውንት መካከል መርጠን መጻሕፍትን እንዲተረጉሙ አድርገን</u> ንባቡን ከነማስረጃው በትርጓሜ አስወጣንለት። ቀጥሎም በግል ገንዘባችን ማተሚያ መኪና ከአውሮፓ አስመጥተንና ማተሚያ ቤት አቋቁመን መጻሕፍቱን ማሳተም ጀመርን።... [እነዚህ] ጥቂቶቹ መጻሕፍት በአብያተ ክርስቲያናትና በየሕዝቡም ቤት እየተነበቡ የሃይማኖት ማጽኛ የመንፈስ ማበረታቻ ሆነው ተገኝተዋል።... የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከመሠረታዊ ቋንቋው ከዕብራይስጥና ከጽርዕ ጋር እየተያየ ሊታረም እንደሚገባው ስለ ተመለከትን ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት <u>ለዚህ ሥራ ተገቢ የሆኑትን ሊቃውንት መርጠን</u> በየካቲት 27 ቀን 1939 ዓመተ ምሕረት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ በቤተ መንግሥታችን ግቢ እንዲቋቋም አደረግን። ኮሚቴውም

ይታያልና። ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በአጠቃላይ በቤተ ክህነት ደረጃ ሳይሆን በአጥቢያም ጭምር ታላላቅ ሕንፃዎች ገንብታ ለንግድ ተቋማት ማከራየቷ ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያን በገንዘብ በኩል ምንም ችግር የሌለባት መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

[28] ከዚህ በፊት የታተሙት የራሷ አይደሉም እያለ መሆኑ ግልጽ ነው። ቀደም ሲል እንደቀረበው ግን ከዚህ በፊት የታተሙት መጻሕፍት በራሷ ሊቃውንትና በቤተ ክርስያቲን ይሁንታ የተተረጉሙና የታተሙ ናቸው።

[29] ወልደ ሚካኤል ቶሎሳ፣ በእንተ ሰማንያ አሐዱ (ዐዲስ አበባ፣ 2005 ዓመተ ምሕረት) ገጽ 15 - አጸንዖት የግል።

[30] ሰማንያ አሐዱ በሚል በ2000 ዓመተ ምሕረት የታተመው መጽሐፍ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ›› ሊባል የማይገባውና ቤተ ክርስቲያን የእኔ መጽሐፍ ነው በሚል ለመገልገያ ልትመርጠው የማትችለው መጽሐፍ መሆኑን ለመመልከት ‹‹ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን›› የሚለውን መጽሐፍ መመልከት ይጠቅማል።

5 ዓመት ያህል በትጋትና በቅንነት ሠርቶ በሚያዝያ 11 ቀን 1944 ዓመተ ምሕረት አቀረበልን።[31]

ይህ ማለት መጽሐፉ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት በሚያምንባቸው ሰዎች የተዘጋጀ ሲሆን መጽሐፉ እንዲታተም የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉትና ተቆጣጣሪ የነበሩት ኃይለ ሥላሴ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አማኝ ብቻ ሳይሆኑ የበላይ ጠባቂ እንደ ነበሩ አንዳንድ መጻሕፍት ይናገራሉ። ስለዚህም መጽሐፉ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት እጅ በቀጥታ ያለበትና ቤተ ክርስቲያንም መጽሐፉ በትክክል የእኔ መጽሐፍ ነው ያለችው መጽሐፍ ነበር ማለት ነው።

ከዚህም በኋላ በ1980 ዓመተ ምሕረት የታተመውና ሰማንያ አሐዱ የተሰኘው ዕትምም ሲወጣ መቅድሙ ላይ የሚከተለውን አስፍሯል፣

> ... [ቀደም ሲል ከ1928 - 1934 ዓመተ ምሕረት የታተመው መጽሐፍ] በውስጡ ከቤተ ክርስቲያናችን የሃይማኖት አባባል ውጭ የሆኑትንና ከግእዙ ጋር የማይስማሙትን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች <u>ቅዱስ ሲኖዶሳችን ከተመለከታቸውና ካስተካከላቸው በኋላ እንደ ገና እንዲታተም አደርግን</u>።... <u>ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በሲኖዶስ አባላት ተመርምሮና ሊስተካከል የሚገባው ተስተካክሎ በዘመነ ፓትርያርክነታችን በአሥራ አንደኛው ዓመት ታተመ</u>።[32]

በዚህ ሐሳብ መሠረት መጽሐፉ የቤተ ክርስቲያናችን ነው ለመባል የሚችል፣ በዘመኑ በነበሩ ሊቃውንት ተመርምሮና ሙሉ በሙሉ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በዚህ መጽሐፍ ላይ ተመሥርቷል የሚል አቋም ባላቸው ሰዎች ጸድቆ የወጣ መጽሐፍ ነው ማለት ነው።

ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ቤተ ክርስቲያን ለበርካታ ዓመታት ሕዝቧን ስታስተዳድርበት የነበረውን መጽሐፍ በማሳተሙ በኩል በቀጥታ እጇ አለበት። ያለ እርሷ ፈቃድ ወይም እውቅና የወጣ መጽሐፍ የለም። ምክንያቱም የታተሙት መጻሕፍት በገዛ ልጆቿ (በሊቃውንቷ) ይሁንታ የወጡ መጻሕፍት ናቸውና። ይህ ብቻ አይደለም ለበርካታ ዓመታት (መጽሐፍ ቅዱስ በዕትመት ለንባብ ከበቃበት ጊዜ ጀምሮ) ይህን መጽሐፍ አንብቡ፣ ይህን መጽሐፍ ታዘዙ፣ ይህ የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ነው፣... ብላ ከፍ አድርጋ ስትሰብከው፣ ስታስተምርበት፣ ሰው ሁሉ የሕይወቱ መመሪያ እንዲያደርገው ስታዘውና ስርዓተ አምልኮ ስትፈጽመበት የነበረው መጽሐፍ ነው።

ትናንትና ትክክል ነው ብላ ስታስተምርበት የነበረውን መጽሐፍ፣ ዛሬ ላይ ተነሥታ ቀደም ሲል የወጡት መጻሕፍት የእኔን አስተምህሮ አይወክሉም፣ ካለች በማታምንበትና የእርሷ ባልሆነ መጽሐፍ በማስተማር ሕዝቡን በብዙ ስሕተት ውስጥ መርታዋለች ማለት ነው። ይህን ያደረገችው ደግሞ በስሕተት ሳይሆን እያወቀች በመሆኑ ሕዝቡን በአደባባይ በድላዋለች። በአደባባይ ለሠራችው ለዚህ ስሕተት በአደባባይ ይቅርታ ልትጠይቅ ይገባል።

---

[31] መጽሐፍ ቅዱስ - የብሉይና የዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (1953 ዓመተ ምሕረት) መቅድሙን ይመልከቱ - አጽንዖት የግል።

[32] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ ሰማንያ አሐዱ (1980 ዓመተ ምሕረት) መቅድሙን ይመልከቱ - አጽንዖት የግል።

ማጠቃለያ

በሁለት ክፍል በቀረበው በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ ማስተላለፍ የተፈለገው ቤተ ክርስቲያን የሌላትን መጽሐፍ (ሰማንያ አሐዱ የሚባለውን) ነው የምቀበለው በማለት ሕዝቡን ቃለ እግዚአብሔርን እንዳያነብ እንቅፋት መሆኗን ነው። በቃልም ሆነ በጽሑፍ የምንቀበለው ሰማንያ አሐዱን ነው ይባል እንጂ ቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነች ሊቃውንቷ ሰማንያ አሐዱ የሚባለው መጽሐፍ ይህ ነው የማለት አቅም የሌላቸው መሆኑ ቀርቧል። ታዲያ ሕዝበ ክርስቲያኑ የቱን መጽሐፍ ያንብብ?

አሁን ገበያ ላይ ያለውንና እንደ ልብ የሚገኘውን መጽሐፍ ገዝተው እንዳያነቡት እሱን አታንብቡ የሚል ስብከት በአደባባይም ጭምር የሚሰበክ ሰብከት ነው። የእኛ አይደለም የሚባለው መጽሐፍ ግን አሁንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን እየተጠቀመችው ያለችውና በራሷ ሰዎች የተዘጋጀ መጽሐፍ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ትናትና ስትጠቀምበት የነበረውን መጽሐፍ ዛሬ የእኔ አይደለም ካለች የትናትናውንም ሆነ የዛሬውን አማኝ አታላዋለች ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ ታላቅ በደል ነው።

አንተ ግን ወገኔ ‹‹ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል›› ተብሎ የተጻፈውን በማስታወስ ዘወትር ቃሉን አንብብ፤ ራስህንም ለቅዱስ ቃሉ አስገዛ (2ኛ ጢሞቴዎስ 3÷16-1)።

ዋቢ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ (1975 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አጭር የታሪክ የሂይማኖት የሥርዓት መጽሐፍ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ሰይፍ የጎተመት እና ማስታወቂያ ሥራ ድርጅት፣ (ሰኔ/ሐምሌ 1991 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ሐዋርያ ኢትዮጵያ</u> ጋዜጣ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (ሐምሌ 1988 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት</u>። ዐዲስ አበባ።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ የቤተ ክርስቲያን ጸሎት (ዐዲስ አበባ፣ 1996 ዓመተ ምሕረት)።

ብርሃኑ ጎበና፣ (ሚያዝያ 1995 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ዓምደ ሂይማኖት</u>። ዐዲስ አበባ፣ አፍሪካ ማተሚያ ቤት።

ዓሥራት ገብረ ማርያም፣ (2005 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ትምህርት መለኮት</u>። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ (1993 ዓመተ ምሕረት - ሁለተኛ ዕትም)፣ <u>ፍኖተ ብርሃን</u>። ዐዲስ አበባ፣ የታተመበት ቦታ ያልተጠቀሰ።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>መርሐ ጽድቅ ባህለ ሂይማኖት</u>። ዐዲስ አበባ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከት ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ (መጋቢት/ሚያዝያ 1982 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ትንሣኤ</u> መጽሔት። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

አሥራት ከበደ (ትርጉም)፣ (2005 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>መጽሐፈ ጦቢት</u>። ዐዲስ አበባ፣ ጎተመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።

መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ (1994 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት</u>። ንግድ ማተሚያ ቤት።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (1995 ዓመተ ምሕረት - ለሁለተኛ ጊዜ የታተመ)፣ <u>ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው</u>። ዐዲስ አበባ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (ዓመተ ምሕረት ያልተጠቀሰ)፣ <u>መጽሐፍ ቅዱስ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን</u> - ልዩ ዕትም መጽሔት። ሳሃ ማተሚያ ቤት።

ወልደ ሚካኤል ቶሎሳ፣ (2005 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>በእንተ ሰማንያ አሐዱ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (1954 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>የብሉይና የዐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (1980 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ</u>። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (2000 ዓመተ ምሕረት)፣ <u>ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ</u>። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ቴዎድሮስ ደመላሽ (ጥር 2010 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ እትም)። <u>ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን</u>። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ሊነበቡ የሚገባቸው መጻሕፍት

ኢየሱስ አማላጅ ነው ማለት ፈራጅ አይደለም ማለት ነውን? እርሱ ራሱ አምላክ ነው፣ ወደ ማን ነው የሚያማልደን? ከእንግዲህ ስለ እናንተ አልለምንም ብሎ የለ? እንዴት አማላጅ ይባላል?

እነዚህና ሌሎችም ጥያቄዎች የተመለሱበት መጽሐፍ

ሰይጣናውያን «ቅዱስ» የሚሉትን መጽሐፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ አዘጋጅተው በምድራችን ላይ መበተናቸውን ተከትሎ መጽሐፋቸው «ቅዱስ» ሊባል እንደማይገባው ይፋ ያደረገ የመጀመሪያው መጽሐፍ



ቤተ ክርስቲያን እንደ ቅዱስ የምትመለከተው ሰማንያ አሐዱ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም ከታሪክ ጋር ያለውን አለመግባባት በማስረጃ የሚያሳይ መጽሐፍ።

መምህር ታሪኩ አበራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ በሆነ ሁኔታ ተአምረ ማርያምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት ያቀረቡት ሰበክት መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ አርቶዶክሳዊ አለመሆኑ የቀረበበት መጽሐፍ

አርሲማ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ስትታይ ከርስቲያን ልትባል ትችላለችን? ለመሆኑ አርሲማ ራሷ ማነች? ሰማዕት የሆነችውስ የክርስቶስ ፍቅር ግድ ብሏት ወይስ...? እነዚህና ሌሎችም ነገሮች የተፈተሹበት መጽሐፍ